የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት

# ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ
# DEBUB NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTHERN, NATIONALITIES AND PEOPLES REGIONAL STATE

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዋሳ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፫

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት ተጠባባቂነት የወጣ

6th Year No. 4
Awassa–4th April, 23, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፴፫/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
የክልሉ የምግብ ዋስትናና የከብት አርቢ አካባቢ የልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፫ ፲፱፻፺፫" ........ ገጽ ፩

## CONTENTS

Proclamation No. 33/2001
"The Southern, Nations, Nationalities and Peoples Regional State Food Security and Pastoral Deevelopment Coordination Office Establishment Proclamation No. 33/2001 ........ Page 1

### የምግብ ዋስትናና የከብት አርቢ አካባቢ የልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በከብት አርቢ አካባቢ በቀጣይነት የተቀናጀ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን የሚያስተባብር አካል መቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በክልሉ የምግብ ዋስትና ሁኔታን በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ አሁን ካለበት ሁኔታ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በደቡብ ብሔሮች ፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ህገ መንግሥት አንቀጽ ፵፱(፫) ሀ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል ።

**፩· አጭር ርዕስ**

"ይህ አዋጅ የክልሉ የምግብ ዋስትናና የከብት አርቢ አካባቢ የልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፫ ፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

**፪· ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡–

፩· "የክልል መንግሥት" ማለት የደቡብ ብሔሮች ፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ማለት ነው ።

፪· "ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ" ማለት የደቡብ ብሔሮች ፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማለት ነው ።

### A Proclamation to Establish the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Food Security and Pastoral Development Coordination Office

Where as, on integrated and organized approach is essential to improve the region food security,

Whereas, it has become necessary to establish a coordinating body for integrated projects progammes that foster the development of pastoral areas,

Now, therefore, in accordance with article 49 sub article 3 (a) of the Constitution of the Southern, Nations Nationalities and Peoples Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short title*

This proclamation may be cited as "The Southern, Nations, Nationalities and Peoples Regional State Food Security and Pastoral Deevelopment Coordination Office Establishment Proclamation No. 33/2001.

2. *Definitions*

Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

1. 'Regional State' means the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State.
2. 'Regional Executive Committee' means the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Executive Committee.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 1.40

፫. "የምግብ ዋስትና" ማለት ሁሉም ሰው ሁልጊዜ በብዛትና በጥራት በቂ ምግብ ማግኘት ሲሆን ይህም ጤናማና ብቃት ያለው ሕይወት እንዲኖረው ማድረግ ማለት ነው።

፬. "አርብቶ አደር" ማለት ለኑሮው መሠረት የሆነውን ገቢ ወይም ምግብ የቤት እንስሳትን ከማርባት የሚያገኝ ሲሆን ለእንስሳቱ የሚሆነው ምግብ በአብዛኛው የሚያገኘው ከተፈጥሮ አካባቢ ነው።

፭. "የአርብቶ አደር አካባቢ" ማለት ማንኛውም የዞን ልዩ ወረዳ የወረዳ ወይም የቀበሌ መስተዳድር ሆኖ አርብቶ አደሩ የሚኖርበት አካባቢ ነው።

፫. መቋቋም

የደቡብ ብሔሮች ፡ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የምግብ ዋስትናና የከብት አርቢ አካባቢ ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ፡ ከዚህ በኋላ "ጽ/ቤት" ተብሎ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የጽ/ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በክልሉ መንግሥት ርዕሰ ከተማ አዋሣ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

፭. አደረጃጀት

ጽ/ቤቱ አንድ ኃላፊና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል ፤

፮. ተጠሪነት

የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል ፤

፯. ዓላማ

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል

ጽ/ቤቱ

፩. በክልሉ የምግብ ዋስትና ሁኔታን በቀጣይነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡

፪. የከብት አርቢ አካባቢን የልማት አቅም ጥናት በማካሄድ የተቀናጀ የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፡

፰. የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ፡-

፩. በክልሉ የረጅም፡ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ የምግብ ዋስትናና የከብት አርቢ አካባቢ ልማት ለማረጋገጥ የሚካሄዱ ሥራዎች እንዲካተቱ ያደርጋል፡ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ተግባራዊ ነታቸውን ይከታተላል፤

፪. የምግብ ዋስትናን በሚመለከት የተለያዩ ጥናቶችን ያካሄዳል ፤ የፖሊሲ ሃሣብም ያመነጫል ፤

፫. የከብት አርቢ አካባቢን የተቀናጀ ልማት በቀጣይነት ለማካሄድ የሚረዱ የጥናት ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ያከናውናል ፤ የአካባቢውን የተለየ የመልማት አቅም በማገናዘብ የልማቱን ጥረት ለመደገፍ የሚያግዙ የፖሊሲ ሃሣቦችን ያመነጫል ፤

፬. በምግብ እጠር አካባቢዎች የህብረተሰቡን የምግብ ዋስትና ሁኔታ ለማሻሻል እንዲቻል የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲጠኑ ያደርጋል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል ፤

፭. በምግብ ዋስትናና በከብት አርቢ አካባቢ በጽ/ቤቱ በኩል የሚካሄዱ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ያስተባብራል ፤

፮. ለተቀናጀ የምግብ ዋስትናና ከብት አርቢ አካባቢ ልማት ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል ፈንድ ወይም ሌላ ሀብት ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከህብረተሰቡ እንዲገኝ ያስተባብራል ፤ የተገኘው ፈንድና ሀብት በክልሉ መንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በህዝባዊ ተቋማት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ፤

3. 'Food Security' means access by all people at all times to sufficient food, in terms of quality and quantity, for an active and healthy life with out loss of such access.

4. 'Pastoralist' means people whose livelihood income being derived from keeping domestic livestock in conditions where most of the feed their livestock eat is natural forage.

5. 'Pastoral Area' means administrative zone, woreda special woredaor kebele where pastoralists live.

3. *Establishment*

The Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State Food Security and Pastoral Development Coordination Office hereafter referred as 'the office' is here by established.

4. *Head Office*

The Office shall have its head office at Awassa, and branch offices at other administrative levels if it seems necessary.

5. *Organization*

The Office shall have a head of the Office, and necessary employees.

6. *Accountability*

The Office shall be accountable to the Regional Executive.

7. *Objectives*

The Office shall have the following objectives:-

1. Cause the preparation and implementation of projects and programmes that are crucial to improve food security in sustainable manner.
2. Prepare and implement integrated development projects and programmes for pastoral areas through understanding their potentials.

8. *Powers and duties of the Office*

The Office:-

1. Cause the incorporation of food security and pastoral development interventions in short, medium and long term plans of the Regional State and upon approval, in collaboration with concerned parties follow up the implementation of same.
2. Undertake studies on food security issues to generate regional policy recommendations.
3. In collaboration with concerned parties, cause studies targeting pastoral areas that are beneficial to generate policy options opted to foster the development of these areas.
4. In collaboration with concerned parties, shall project proposals of employment opportunity schemes targeting food insecure localities, upon approval follow up the implementation of same.
5. Coordinatefood security and pastoral developmental interventions that are initiated by the Office.
6. Shall invalve in securing funds resources from government, Non Governmental Organizations and community for implementation of integrated food security and pastoral development projects programmes. The Office shall facilitate the use of available funds by government, non-government and local institutions.

፯. ዓላማውን ለማስፈጸመ ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤

፰. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በተለያዩ ደረጃዎች ያቋቁማል።

፱. ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፤

፲. በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል እንዲሁም ከሥራ ያሰናብታል።

፲፩. ከሥራ አስፈጻሚ ኮሙቴ የሚሰጠውን ተመሳሳይ ሥራዎች ያከናውናል፤

፱. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

፩. የጽ/ቤቱ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ለጽ/ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፪. የጽ/ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤

፫. የጽ/ቤቱን በጀት በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

፬. ጽ/ቤቱ ከሌሎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ጽ/ቤቱን ይወክላል፤

፭. በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ከሥራ ያሰናብታል፤

፮. ከጽ/ቤቱ ሥራ ጋር የተያያዙና ከክልሉ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፤

፲. በጀት

የጽ/ቤቱ የበጀት ምንጭ ከሚከተሉት ይሆናል፤

፩. ከክልሉ መንግሥት የሚመደብ

፪. ከእርዳታ ወይም ስጦታ የሚገኝ

፫. ከሌሎች

፲፩. የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብት

፩. ጽ/ቤቱ የተሟላ የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብትን ይይዛል።

፪. የጽ/ቤቱ የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብት በክልሉ መንግሥት ዋናዉ ኦዲተር ወይም እሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ ።

፲፪. መመሪያ ስለማውጣት

ጽ/ቤቱ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው

፲፫. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ፤ ደንብ ፤ መመሪያ ወይም የአሠራር ሁኔታ በዚህ አዋጅ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፲፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከዛሬ ሚያዝያ ፲፭/፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

— ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

አባተ ኪሾ

የደቡብ ብሔሮች ፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች

ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር



7. Shall make relation with others to achieve the objectives.
8. In collaboration with other concerned bodies, shall establish branch offices at different levels as may be necessary.
9. Shall prepare and submit performance report to the Executive Committee and other concerned bodies.
10. Shall employ, administer and dismiss employees in accordance with civil service laws.
11. Shall perform other similar tasks to be vested by the Executive Committee.

9. *Powers and duties of the Office head*

1. According to article 8 of this Proclamation, the Office head shall implement the powers and duties vested for the Office.
2. Shall direct, administer and supervise the activities of the Office.
3. Shall prepare the budget of the Office and submit to the Regional State, upon aooroval implement same.
4. Can represent the Office in all its dealings with other parties.
5. Can delegate part of his duties and responsibilities to the concerned department heads and other employeesof the Office to the extent necessary to facilitate for effective execution of duties and responsibilities of the Office.
6. Shall perform similar tasks to be given by the Executive committee.

10. *Budget*

The budget of the Office shall be from the following sources:-

1. Budget allocated by the Regional State
2. Money or resources obtained from donors
3. Money or resources obtained from other sources

11. *Books of account*

1. The Office shall keep complete and accurate books of account.
2. The Regional State's Auditor General or auditors designated by him shall audit the books of account of the Office annually.

12. *Powers to essue guidelines*

The Offices has been given a mandate to issue guidelines that are necessary for the implementation of this Proclamation

13. *Inapplicable laws*

Any law, regulation, guideline or working practice inconsistent with this proclamation, shall be in plicable on matters provided herein.

14. *Effective date*

This proclamation shall come into force as of the 23rd day of April 2001.

Done at Jinka this 23rd day of April 2001.

ABATE KISHO

President of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State